# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 86 ታህሳስ 29 2002 ዓ.ም


## ወያኔ ሰራዊት ለመቅጠር ማስታወቂያ አወጣ፣ ምላሹ ግን አሉታዊ ነው ተባለ

የዘረኝነት ፖሊሲውን በመቃወም መከላከያ ሰራዊትን ጥለው የሚጠፉ የሰራዊት አባላት ቁጥር መበራከት ያስደነገጠው ወያኔ፣ ሰራዊት ለመቅጠር ማስታወቂያ ማውጣቱን ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ ዘግቦአል። በዘገባው መሰረት የመከላከያ ሰራዊትን ለመቀላቀል የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን በየወረዳ ጣቢያዎች በሚገኙ የደህንነት ጽፈት ቤቶች ሄደው ይመዘገባሉ።

የውስጥ ምንጮችን ጠቅሶ የቀረበው ሪፖርት እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አስፈሪ ሁኔታ ወያኔን በእጅጉ እንቅልፍ ነስቶታል። "በሰሜን ኢትዮጵያ በኤርትራ በኩል ተቃዋሚዎች ጦርነት ሊቀሰቅሱብን እየተዘጋጁ ነው ፣በምስራቅ በኩል ከአልሻባብና ከኦጋዴን ነጻ አውጭ ግምባር ከፍተኛ አደጋ ተደቅኖብናል" እያለ በመቀስቀስ ላይ የሚገኘው ወያኔ፣ በነባሩ የሰራዊት አባላት ላይ ያለው እምነት መመናመን አዳዲስ የሰራዊት አባላትን ለመመልመል አስገድዶታል። በተለያዩ ግምባሮች ለውጊያ የሚላኩ የሰራዊት አባላት ተቃዋሚዎችን መቀላቀላቸው ወይም በየጊዜው እየከዱ ወደ ኬንያ፣ የመንና ወደ ሌሎች ጎረቤት አገሮች መሄዳቸው ለወያኔ ተጨማሪ ራስ ምታት እንደፈጠረበት ሲታወቅ ፣ ሰሞኑን ወያኔ በመቀሌ ለተገኘው የሱዳን መንግስት ልኡክ ያቀረበው ተማጽኖ የዚሁ በሽታ መገለጫ መሆኑንም ሪፖርተራችን አክሎ ገልጿል።

**(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የነጋዴው ማህበረሰብ በሚጣልበት ተደጋጋሚ ግብር እጅግ መማረሩ ተገለጸ

ላለፉት አምስት ተከታታይ አመታት የንግዱን ማህበረሰብ ቁም ስቅል ሲያሳየው የከረመው ወያኔ፣ ሰሞኑን ደግሞ ቫት የተባለውን ግብር ባነስተኛ ነጋዴዎች ላይ ለመጣል የሚያደርገው ሩጫ የንግዱን ማህበረሰብ ክፉኛ አስቆጥቶታል።

ከዚህ ቀደም አመታዊ ሽያጫቸው ከ ግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ሰዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ቫት እንዲከፍሉ ሲደረግ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን፣ አሁን ግን ፖሊሲው ተቀይሮ ሽያጫቸው ከስድስት መቶ ብር በላይ የሆኑ የንግድ ድርጅቶች ቫት እንዲከፍሉ እየተደረገ እንደሆነ የአዲስ አበባዋ ሪፖርተራችን ዘግባለች።

"ተጨማሪ እሴት ታክስ በመሰረቱ ነጋዴውን ማህበረሰብ ሳይሆን ህዝቡን ነው በቀጥታ የሚጎዳው" የምትለው ዘጋቢያችን፣ አሁን በሚታየው የኑሮ ውድነት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣል፣ ህዝቡን ለመግደል ካልሆነ ሌላ ምንም አላማ የለውም" ስትል የህዝቡን ስሜት ለማሳየት ሞክራለች።

ነጋዴው ማህበረሰብ የሸማቹን ማህበረሰብ ምሬት እየሰማ ምንም ለማድረግ አለመቻሉን የገለጸችው ዘገባያችን፣ ወያኔ ገንዘብ እያጠረው በመጣ ቁጥር በነጋዴውና በህዝቡ ላይ የሚፈጥረው ጫና ህዝቡን ለተቃውሞ ሊያስነሳው እንደሚችልም ጠቁማለች ።

## በመደናበርና በጭንቀት ላይ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ከመገደል ሙከራ ተረፍን ሲሉ አስታወቁ

ባለስልጣናቱ ከዚህ ቀደም በጄኔራል ተፈራ ማሞ የተመራ ሀይል ጥቃት ሊያደርስብን ነበር ሲሉ የፈጠራ ድራማዎችን እጅግ በወረደ መልኩ መስራታቸውና ለህዝብ ማስተላላፋቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ትናንት ደግሞ የአርበኞች ግምባር የተባለው ድርጅት አባላት ከኤርትራ መንግስት ጋር በመተባበር የመግደል ሙከራ ሊያደርጉ ሲሉ ተያዙ ሲል እንደልባቸው በሚቆጣጠሩት ቴሌቪዥን ተናግረዋል።

የአዲስ አበባው ወኪላችን "ሰዎቹ የመገደል ሙከራ ተደረገብን እያሉ በተደጋጋሚ ማቅረባቸው ምን ያክል በፍርሀት ውስጥ እየኖሩ እንደሚገኙ ያሳያል፤ የኢትዮጵያ ህዝብ መለስ ዜናዊ ና ግብረአበሮቹ ቢጠፉለት ይደሰታል እንጅ እነሱ ጠፉ ብሎ ሀዘን አይቀመጠም" ሲል ያነጋገራቸውን ሰዎች ዋቢ አድርጋ ገልጻለች ።

ዘጋቢአችን "ልክ ህዝቡ የሚወዳቸው ይመስል የመገደል ሙከራ ሊደረግብን ነበር እያሉ በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይሰማል፤ ለመሆኑ የትኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው መለስ ዜናዊ ወይም በረከት ስምኦን ሊገደሉብን ነበር ብሎ በቁጭት የሚነሳው? ህዝቡማ ገና ድሮ በቃችሁን ብሎአል" ስትል የህዝቡን ስሜት ለመግለጽ ሞክራለች።

ላለፉት 19 አመታት በፍርሀት ቆፈን ተይዞ አንድም ቀን በነጻነት ከህዝብ ሳይቀላቀል እድሜውን የጨረሰው መለስ ዜናዊ ፣ ከባድ መሳሪያዎችን በያዙ ቅልብ ወታደሮች 24 ሰአት እየተጠበቀ እንኳን አሁንም በስጋት ውስጥ መገኘቱ፣ ሰውየው በአእምሮ መረበሽ ውስጥ ለመሆኑ ማስረጃ ነው የሚል አስተያየቶችም መስጠታቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል።

መለስ ዜናውን በአለም ላይ ካሉት ጨካኝ አምባገነኖች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው ከህዝብ ሳይገናኝ ለ19 አመታት በዋሻ ውስጥ መቀመጡ ሲሆን፣ በዚህ ድርጊቱም "ፈሪ አምባገነኖች" ከሚባሉት ገዢዎች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀስ ይሆናል።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በእነ ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ የተወሰደው እርምጃ የአማራውን ህዝብ ለትግል እያነሳሳው መሆኑ ታወቀ፣ እርምጃ መወሰድም ተጀመረ

የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ በእነብርጋዲየር ጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ የወሰደው እርምጃ በአማራው ህዝብና አማራ በሆኑት የሰራዊቱ አባላት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ቁጣ ቀስቅሷል። በአንዳንድ የአማራ ክልል አካባቢዎች ህዝቡ በወያኔ ንብረቶችና የወያኔ ሰላዮች በሆኑ ግለሰቦች ላይ እርምጃ መውሰድ መጀመሩንም ለማወቅ ተችሎአል። ታህሳስ 22 ቀን 2002 አም በጎንደር ክፍል ሀገር በአዲስ ዘመን ከተማ ንብረትነቱ የህወሀት የሆነ የነዳጅ ማመላለሻ ቦቴ መኪና እስከነዳጁ በፈንጅ ተመትቶ የጋየ ሲሆን፣ በዚሁ ከተማ በህዳር ወር መጫረሻ ደግሞ ማንነታቸው ያልታወቁ ሰዎች በጣሉት ፈንጅ ሁለት የህወሀት ሰላዮችና ካድሬዎች ተገደለው አምስቱ ደግሞ ክፉኛ ቆስለዋል። በአማራ ክልል በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ጸረ ወያኔ የሆኑ እንቅስቃሴዎች በስፋት መታየትመጀመራቸውንና ሊፈነዱ መቃረባቸውንም ሪፖርተራችን ከባህርዳር ዘግቧል።

በተያያዘ ዜናም በወያኔ እስርቤት ውስጥ ባሉት በእነ ብርጋዲየር ጄኔራል ተፈራ ማሞና በሌሎችም እስረኞች ላይ ቅጠቀጣ የፈጸሙትና ክብራቸውን በሚነካ መልኩ ብልግና የተሞላበትን ዘረኛ ስድብ የሚሳደቡት መርማሪ ተብየዎች በቀጥታ ከትግራይ ክልል የመጡ ታማኝ የህወአት የደህንነት ሰዎች መሆናቸው ታውቋል። ሰዎቹ በጨካኝነታቸው ከበረሀ ጀምሮ የሚታወቁ መሆናቸውን የደረሰን መረጃ አመልክቶ፣ በእስር ላይ የሚገኙትን የአማራ ተወላጆች ዘርንና ማንነታቸውን እያንቋሸሹ እንደእባብ ሲቀጠቅጧቸው እንደነበር ለማወቅ ተችሎአል።

የመረጃ ምንጫችን አክሎ እንደዘገበው በህግ ስም የቀረበው ሞትና የእድሜ ልክ ጉደኛ ውሳኔ የተወሰነው መለስ ዜናዊ፣ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ተብየው አባይ ጸሀየ፣ የደህንነት ሀላፊ ተብየው ጌታቸው አሰፋ፣ የኮሚኒኬሽን አማካሪ ተብየው በረከት ስምኦንና ኢታማጆር ሹም ተብየው ሳሞራ የኑስ ና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንትና የመለስ ዜናዊ የህግ አማካሪ መንበረ ጸሀይ ታደሰ ባደረጉት ስብሰባ ሲሆን፣ ስብሰባውንም ያካሄዱት የሌሎች ብሄር ተወላጆችን ሆን ብለው በማግለል በትግረኛ ቋንቋ እንደነበር የደረሰን መረጃ አመልክቷል። እነዚህ ሰዎች ተሰባስበው የወሰኑት ውሳኔ ሶስት ዘርፎች እንዳሉትም ለማወቅ ችለናል።

የመጀመሪያው እቅድ እጅግ ታማኝ በሆኑ የትግራይ ተወላጅ የደህንነት አባላት የሚመራ የስለላ መረብ በአማራ ክልል መዘርጋት ሲሆን ሁለተኛም እቅድ ደግሞ በክልሉ የሚቀሰቀስ አመጽ ካለ አስቀድሞ ለመምታት የሚችል የፈጥኖ ደራሽ ሀይል በክልሉ ማሰልጠንና ማደራጀት ነው። በሶስተኛ ደረጃም የአማራውን ክልል ህዝብ ቀልብ ሊገዙ የሚችሉ አንዳንድ የናሙና ስራዎችን በክልሉ በመስራትና ወያኔ በእነ ጄ/ል ተፈራ ማሞ ላይ የወሰደው እርምጃ የአማራውን ህዝብ ለመምታት አስቦ ያደረገው አለመሆኑን የሚያሳይ የፕሮፓጋንዳ ስራ መስራት የሚል መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።

በዚሁም መሠረት የስለላ መረቡን ከክልል እስከ ቀበሌ የመዘርጋቱ ሂደት እንደተጠናቀቀ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## በአማራ ክልል ሶስት ንጹህ ዜጎች በወያኔ ፈጥኖ ደራሾች ተገደሉ

ሽፍታ ታደራጃላችሁ የተባሉ ሶስት የምስራቅ ጎጃም አካባቢ ተወላጆች በወያኔ ፈጥኖ ደራሽ ወታደሮች መገደላቸውን የአማራ ክልል የግንቦት7 ዘጋቢ ገለጸ። በምስራቅ ጎጃም ጃቢ ጠናን ወረዳ ነዋሪ የነበሩት የሸዋስ አስናቀ፣ ምትኩ ባያብልና አስማማው አወቀ የተባሉት ግለሰቦች የተገደሉት ፣ ሽፍቶችን ታደራጃላችሁ፣ በአካባቢው ለሚንቀሳቀሱት ነጻ አውጭ ነን ባዮች መረጃ ታቀብላላችሁ፣ ህዝቡን ላመጽ ትቀሰቅሳላችሁ ተብለው ሲሆን፣ ርምጃውም የተወሰደባቸው በአካባቢው በሚገኝ አንድ ገደላማ ቦታ ነው። የፈጥኖ ደራሽ አባላቱ እርምጃውን ከወሰዱ በሁዋላ ማምሻውን አካባቢውን ጥለው መሄዳቸውን የአገኘነው መረጃ አመልክቶ፤ ፈጥኖ ደራሾቹ ሰዎችን ከየቤታቸው እየለቀሙ በሚወስዱበት ጊዜ "ወደ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ነው የምንወስዳችሁና ዝም ብላችሁ ተከተሉን" ብለው እንዳሉዋቸው፣ ከተወሰኑ ሰአታት በሁዋላ የተኩስ ድምጽ መሰማቱን፣ በማግስቱም ሰዎቹ ሞተው መገኘታቸውን ያገኘነው መረጃ አመልክቷል።

የአካባቢው ህዝብ ለቀበሌው ታጣቂዎች ጥያቄ ሲያቀርብ "ነጻ አውጭዎች ናቸው የገደሉዋቸው፣ በቅርቡ አድነን እንይዛቸዋለንና ተረጋጉ" የሚል መልስ እንደሰጡዋቸው፣ ሆኖም ግን ህዝቡ እናንተ ናችሁ የገደላችሁዋቸው እንጅ ነጻ አውጭዎች አይደሉም የሚል መልስ መስጠቱን ለማወቅ ተችሎአል።

በአማራ ክልል የተለያዩ ቀበሌዎች በርካታ ግድያዎችና እስራቶች እየተፈጸሙ እንደሚገኙ ሪፖርተራችን አክሎ ገልጿል።

## መለስና ግብረአበሮቹን ለፍርድ ሳናቀርብ እንቅልፍ ባይናችን አይዞርም!!!

1. በግንቦት7 አመራር አባላትና በነጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ የተሰጠው የፈሪ ዱላ የሞትና የእድሜ ልክ እስርና እንዲሁም ፍጹም ጭካኔ የተሞላበት አያያዝ፤
2. በወያኔ ቴሌቪዥንና ራድዮኖች ስለ ግንቦት7 የሚነገረው ማስታወቂያ አይሉት ማስፈራሪያ፤
3. ሰፋፊ ለም መሬቶችን ለባዕዳን ለመሸጥ የሚደረገው ሩጫ እና ከገዢዎቹም መካከል የጎረቤት አገራት መንግሥታት ከፍተኛ ሹማምንትና ቤተሰቦቻቸው የሚገኙበት መሆኑ፤
4. ከሱዳን መንግሥት ጋር የሚደረገው የዝግ በር የመሬት ድርድር እና የመቀሌ "በሩን ዝጋልኝ" በጭፈራ ሳይቀር የታገዘ ልምምጥ፤
5. ኪሱ ውስጥ ባልገቡ ሰላማዊ ታጋዮችና ጋዜጠኞች ላይ በየእለቱ እየከፋ የመጣው ወከባ፤
6. መረን ያጣው የወያኔ የጅምላ የአባላት ምልመላ፤
7. በሃገሪቱ ዴሞክራሲ ያለ ይመስል ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ሊደረግ እንደሚችል ለማሳመን የሚከወነው የአምባገነኖች የማጭበርበር ድራማ፤ እና
8. በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን ከቸነፈር ሲኦል ደጃፍ ላይ ገትሮ "የልማት መንግሥት ነኝ" የሚለው ይሉኝታ የሌለው ቅጥፈት።

ከላይ የተዘረዘሩት እርስ በርሳቸው ያልተያያዙ የተናጠል ጉዳዮች ቢመስሉም ባንድ ላይ ሲታዩ የሚሰጡት አጠቃላይ ስዕል በወያኔ ሰፈር ያለውን መረበሽ ነው።

አምባገነኖች መውደቂያቸው ሲደርስ ሁሉም ነገር በቁጥጥራቸው ሥር ያለ ለማስመሰል መቅበጥበጣቸው የተለመደ ነው። የወያኔም መቅበጥበጥ ምክንያቱ መሠረቱ እየተናደ በመሆኑ ነው። ይሁን እንጂ እንደማንኛውም አምባገነን መለስ እየወደቀም ቢሆን ሁሉም ነገር በመዳፍ ውስጥ ያለ ማስመሰል ይፈልጋል። ቢቻለው መንጋትና መምሸትም ሳይቀር በሱ መልካም ፈቃድ የሚከናወን መሆኑን ብናምንለት ደስታው ነው። ይህ የሁሉም አምባነኖች የመውደቂያ ወቅት መለያ ባህርይ ነው።

አምባገነኖች ዞር ብሎ የሚያይ አዕምሮ ስላልፈጠረባቸው ከቀደምቶቻቸው ትምህርት አይቀስሙም፡፡ ዘረኛ የሆኑ አምባገነኖች ደግሞ ከሌሎቹ አምባገነኖች የባሰ ድፍን ጭንቅላት ያላቸው በመሆናቸው በእዚያው ልክ ከታሪክ የመማር እድላቸው ጠባብ ነው፡፡ ታሪክ እንደሚያሳየን የሕዝብ የነፃነት ትግል ሲያይልባቸው ወታደራዊ ጡንቻቸውን በማደለብ ከውድቀት የተረፉ አምባገነኖች የሉም፡፡ የሕዝብ ብሶት ሲጨምር የስላላ መዋቅራቸውን በማስፋት ሕዝብን ለዘላለሙ ማፈን የቻሉም በታሪክ አይገኙም፡፡ ሕዝብ እየተራበ ሃገር ጥጋብ ነው ብለው ለራሳቸው የካዱ አምባገኖች ጠኔ ይዞት ወደ ከርሰ መቃብር ከሚገባው ደሃ ሕዝብ ጋር ሲቀበሩ እንጂ፣ ሥርዓታቸው ሲፈካና ሲያብብ አልጋቸውም ሲጠና አልታየም። ሕዝብ በአይኑ የሚያየውን በጆሮው የሚሰማውን በእጁ የሚዳስሰውን በመካድ በሃሰት ፕሮፓጋንዳ ዓይን ጨፍንና ላሞኝህ ያሉ አምባገነኖች መጨረሻቸው የፈለገው ነገር ቢናገሩ በሕዝብ የማይደመጡ፤ በሕዝብ የተተፉ ብቸኛ እና አሳዛኝ ሞት የሚሞቱ ናቸው፡፡ ወያኔ አምባገነን ነውና እጣው በታሪክ ከታዩት አምባገነኖች የተለየ አይሆንም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለአምባገነኖች ባህርይ እና የመጨረሻ እጣ ከበቂ በላይ እውቀትና ግንዛቤ ያለው በመሆኑ ወያኔ አይበገሬ ለመምሰል በሚያደርገው መቅበጥበጥና ሁሉን–አዋቂ ሁሉን–ፈፃሚ ሆኖ ለመታየት በሚያደርገው መፈራገጥ ግራ የሚጋባ አይደለም – የነፃነት ታጋዮችም እንደዚሁ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቀን ወደ ቀን እየናረ መያዣና መጨባጫ በሌለው የወያኔ ዘረኞች መቅበጥበጥ ከቶውኑ አይደናገርም – የነፃነት ታጋዮችም እንደዚያው፡፡ ይልቁንስ ሕዝብ ወያኔ አንገት ውስጥ ያጠለቀውን ማነቆ ይበልጥ በማጥበቅ ከዚህም በላይ ተቅበጥብጦና ተወራጭቶ እንዲያበቃለት ትግሉን ያጦዛል እንጂ በቅጥፈት፣ ሃኬት፣ ቱልቱላና ድንፋታ አይፈታም – የነጻነት ታጋዮችም እንደዚሁ፡፡

**አምርረነናል!!!** መለስና ግብረአበሮቹን ለፍርድ አቅርበን ለነፃና ፍትሃዊ ሥርዓት መሠረት ሳንጥል እንቅልፍ ባይናችን አይዞርም ብለናል!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## በእነ ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ . . . ከገጽ 1 የዞረ

የአማራ ክልል ታማኝ የትግራይ ተወላጅ የህወሀት አባላት የሚመሩዋቸው ከ500 በላይ የስለላ ተቋማት ተዋቅረው ስራቸውን በመስራት ላይ ናቸው። ተቋማቱ ማን ምን እንደተናገረ በመመዝገብ፣ ወያኔን ተችተዋል የተባሉ ሰዎችን በማፈን፣ በመደብደብና በመግደል ስራ ላይ መሰማራታቸውን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፣ በክልልሉ ውስጥ የሚገኙ በርካታ የወያኔ ተቃዋሚዎች ታፍነው በመወሰድ ላይ ናቸው። በአማራው ክልል የሚነሱ ተቃውሞዎችን የሚመታውና የትግራይ ተወላጆች ብቻ የሚያዙት ልዩ የፈጥኖ ደራሽ ሀይልም በቅርቡ ስልጠናውን ጨርሶ መመረቁን ምንጫችን አክሎ ገልጿል። ወያኔ በአማራው ክልል ይህ ነው የሚባል የልማት ስራ ባይሰራም በጃፓን እርዳታ የሚሰራውንና የወያኔ ባለስልጣናት ከፍተኛ የሆነ የኮሚሽን ገንዘብ ያገኙበትን የአባይ ድልድይ ለአማራው ህዝብ ልማት ታስቦ እንደተሰራለት አድረገው ለማቅረብ እየሞከሩ ነው።

በበረከት ስምኦን የሚመራው የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ክፍል ካለፈው ዕሁድ ታህሳስ 24 ጀምሮ በእነጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ ያሳየው የተቀነባበረ የሀሰት ፊልም የፕሮፓጋንዳው አነድ አካል መሆኑን ምንጫችን አክሎ ገልጿል።

ይህ ሁሉ በሆነበት ጊዜ ግን የአማራው ህዝብ የወያኔውን ዘረኛ ሀይል ለማስወገድ ቆርጦ በመነሳት ላይ መሆኑን የሚደርሱን መረጃዎች አምልክተዋል። ህዝቡ ከእንግዲህ ከወያኔ አገዛዝ ጋር እንደማይቀጥል፣ ወያኔን ባለ በሌለ ሀይሉ ለመፋለም እየወሰነ እንደሚገኝ የግንቦት7 የመረጃ ምንጮች ተናግረዋል። የህዝቡ ቆራጥ እንቅስቃሴም የወያኔን መሪዎች እያስደነገጠ መምጣቱን ለማወቅ ተችሎአል።

በተያያዘ ዜናም በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ የትግራይ መኮንኖች ፍጹማዊ የበላይነት ያንገፈገፋቸው የጦር አባላት ቁጥር እየተበራከተ መምታት ያስደነገጠው ወያኔ ከአማራ ተወላጆች በተጨማሪ የኦሮሞና የሌሎችም ብሄር ተወላጆችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ዝግጅትም እያደረገ እንደሆነ የግንቦት 7 የመከላከያ ምንጮች ዘግበዋል። ወያኔ ህገመንግስቱን ና የህወሀትን ፖሊሲዎች ለሰራዊቱ እንደአዲስ ማስጠናት መጀመሩን የጠቀሰው ምንጫችን፣ በዚሁ ጊዜ "ህገ መንግስቱ እየተከበረ አይደለም፣ ሙስና ተስፋፍቷዋል፣ የትግራይ ብሄር ፍጹም የበላይነት ነግሷል" የሚል ጥያቄ ያቀረቡ የአማራና የሌሎች ክልል ተወላጆች የሰራዊት አባላት እየተለቀሙ ወደአልታወቀ ስፍራ ተወስደዋል።

እንዲሁም በጉርጂ አካባቢ የተነሳው ህዝበዊ ተቃውሞ ቀጥሎ አካባቢው በፌደራል ፖሊሲችና የመከላከያ አባላት መከበቡን የኦሮሚያ ክልል ምንጫችን ገልጿል። ባለፈው ሳምንት አመጹን አነሳስታችሁዋል የተባሉ ተማሪዎችና አንዳንድ ታዋቂ ግለሰቦች ተይዘው ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸውን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን፣ ህዝቡም ሰዎቻችንን አምጡ የሚል ጥያቄ በተደጋጋሚ እያሰማ መሆኑ ታውቋል። ይህ አመጽ በመገናኛ ብዙሀን እንዳይተላለፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሲያደርግ የነበረው ወያኔ፣ የግንቦት7 ድምጽ መረጃውን እንዴት ሊያገኝ ቻለ "በመካከላችን ሰርጎ ገቦች አሉ ማለት ነው" ሲሉ የክልሉ ባለስልጣናት መነጋገራቸውን ሪፖርተራችን ዘግቧል። የግንቦት 7 ድምጽ ዜናው ለህዝብ ይፋ ካደረገ ቦኋላ ሪፖርተር የተባለው የወያኔ አፈቀላጤ የሆነው ጋዜጣ ባለፈው እሁዱ ህትመቱ ሰፊ የዜና ሽፋን ሰጥቶት ዘግቦታል። በአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች የተከሰቱትን ተመሳሳይ አለመረጋጋት ዘግቦ የማያውቀው ሪፖርተር ይህንን ዜና ሽፋን ለመስጠት የሞከረው ምናልባትም ተቃውሞው በከፊል አላሙዲን የተባለውን የወያኔ ባለሀብት ስለሚመለከትና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሁለቱ የወያኔ ሰዎች መሃል እየጎላ በመጣው ልዩነት ሰበብ ይሆናል የሚሉ አስተያየቶች ተሰምተዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ በጎንደር ዩኒቨርስቲ በተነሳው ተቃውሞ በርካታ ተማሪዎች መቁሳለቸውን ሪፖርተራችን ከስፍራው ዘግቧል። የተቃውሞው መነሻ በግልጽ ባይታወቅም ባለፈው እሁድ ታህሳስ 25 ቀን 2002 አም የፌደራል ፖሊሶች ግቢውን በመውረር በተማሪዎች ላይ ጥቃት ሲሰነዝሩ የትግራይ ተወላጅ ተማሪዎች ከፌደራል ፖሊሶች ጎን በመቆም በአማራ ተማሪዎች ላይ ድብደባ ፈጽመዋል። በድርጊቱ የተበሳጩ የአማራ ተወላጅ ተማሪዎችም በትግራይ ተወላጅ ተማሪዎች ላይ የአጸፋ ርምጃ በመውሰድ በተወሰኑት ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ታውቋል። በሁለቱም ወገኖች ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎች መኖራቸውንና ይህን ዘገባ እስካጠናከርንበት ጊዜ ድረስ ትምህርት አለመጀመሩንም ለማወቅ ችለናል። በትግራይ ና በአማራ ተወላጅ ተማሪዎች መካከል ከፍተኛ የሆነ ፍጥጫ መኖሩንና በማንኛው ጊዜ ሊፈነዳ እንደሚችል ሪፖርተራችን አክሎ ዘግቧል።

**በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

**የፖስታሳጥን ቁጥር :-** POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 86 ታህሳስ 29 2002 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# ፕሬዚዳንት ኦባማ ኦስሎ የኖቤል ሽልማት ስነስርአት ላይ ተገኝተው ያደረጉት ንግግር በግርድፉ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ እንደሚከተለው ቀርቦአል

## ክፍል 2 ካለፈው የቀጠለ (የመጨረሻ ክፍል)

ይህንም ያደረግነው የኛን ፍላጎት ጫና በማድረግም አይደለም። ይህንም ያደረግነው መልካም ከሆነ ውስጣዊ ስሜት የተነሳ ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን የተሻለ ዓለምን ከማስረከብ ፍላጎት አንጻር ሲሆን፤ የነዚህ ሃገራት ዜጎች ልጆችና የልጅ ልጆች በነጻነትና የተመቻቸ ህይወት ዉስጥ መሆን ለልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን የተሻለ ህይወትን ያመጣል ብለን ስለምናምን ነው።

በመሆኑም አዎን፤ የጦርነት ሂደቶች ሰላምን ባለበት ሁኔታ ጠብቆ የማቆየት ሚናን ሊጫወቱ ይችላሉ። በዚህም ላይ ይህ እዉነታ ሊነጣጠል በማይችል መልኩ ከሌላው ጋር ሊኖር የግድ ይላል- ይህም ፍትሃዊም ይሁን ፍትሃዊ ያልሆነ፤ ጦርነት በሰው ልጅ ላይ አሳዛኝ ዉጤትን ማስከተሉ አይቀሬ ነው። ለወታደር ወኔና መስዋዕትነት በክብር የተሞላ፤ የሃገር ፍቅርን መግለጫና ወታደራዊ ጓድነትን ማረጋገጫ ነው። ይሁን እንጂ ጦርነት በራሱ ብቻዉን ክብርና ዝና ባለመሆኑ ፍጹም የግድ የሚፈለግ ነገር አይደለም።

በመሆኑም ፈታኝ የሆኑት ችግሮቻችን በከፊል ከነኝህ የማይነጣጠሉ የሚመስሉ እውነታዎች- ማለትም ጦርነት አንዳንድ ጊዜ አስፈላጊ መሆኑን እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ ጦርነት የሰው ልጅ ትርጉም የለሽ ድርጊትነቱ ጋር የተያያዙ ናቸው። ተጨባጭ በሆነ መልኩ ሁሉንም ጥረቶቻችንን ወደ አንድ ቀደም ብሎ ፕሬዘዳንት ኬኔዲ አቅርበውት ወደነበረ ተግባር ማምጣት አለብን። " ሁላችንም ትኩረት እናድርግ" አሉ ኬኔዲ "ወደ ተሻለ ተግባራዊ፤ ልንደርስበት ወደምንችለው ሰላም፣ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ ቅጽበታዊ አብዮትን በማካሄድ ሳይሆን በሰው ልጅ ተቋማት ላይ አዝጋሚ የሆኑ ተጨባጭ ለውጦችን በማምጣት ላይ"። ይህ አዝጋሚ ሂደት ምን ሊመስል ይችላል? እነዚህስ ተግባራዊ ርምጃዎች ምን ሊሆኑ ይገባቸዋል?

በመጀመሪያ፤ እኔ እንደማምንበት ሁሉም ሃገራት- ጠንካሮችም ይሁኑ ደካሞች- ራሳቸዉን ገዥ ከሆነው ደረጃውን የጠበቀ የሃይል አጠቃቀም ጋር ሊያዛምዱ ይገባቸዋል። እኔ- ልክ እንደማናቸዉም ሃገራት መንግስታት መሪዎች- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሃገሬን ከጥቃት ለመከላከል በተናጠል ተግባራዊ ላደርገው የሚያስችል መብት አለኝ። ይሁን እንጂ ራስን ደረጃዉን ለጠበቀ የሃይል አጠቃቀም ተገዥ ማድረግ፤ ዓለማቀፋዊ ለሆነ ደረጃ፤ ራሳቸዉን ተገዥ ላደረጉ ጥንካሬን ሲሰጥ ራሳቸዉን ተገዥ ለማያደርጉት ግን ደካማነትን ብሎም መነጠልን ሊያስከትል እንደሚችል አምናለሁ።

በሴፕቴምበር 9/ 11 በአሜሪካ ላይ ስሜት የለሽ ጥቃት ከደረሰ በኋላ ቀሪው ዓለም ከአሜሪካ ጎን በመቆም ሽብርተኝነትን ለማስቆም በሚደረገው ርብርብ ድጋፉን የሰጠ ሲሆን አሁንም ለዚሁ ተግባር አፍጋኒስታን ላይ እየተደረገ ላለው ሽብርተኝነትን የማስወገድና እውቅና ያለውን ራስን ከጥቃት የመከላከል መርህ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። በተመሳሳይ መልኩ ኩዌት በተወረረችበት ወቅት የዓለም ህብረተሰብ ሳዳም ሁሴንን የመጋፈጥ አስፈላጊነትን ተገንዝቦ ነበር- ይህም ተግባር በአንድ ሃገር ላይ የጉልበት ወረራ መፈጸም ሊያስከፍል የሚችለዉን ዋጋ በግልጽ አሳይቶ አልፏል።

እናም ይህ በተለይ ወታደራዊ ርምጃ ራስን ከመከላከል ባለፈ መልኩ ሲካሄድ ወይም አንድ ተወራሪ ሃገር ከወራሪው ሃገር ራሱን ለመከላከል በሚያደርገው ጥረት ሂደት ጠቀሜታው ይታያል። ከዚህም በበለጠ፣ ሁላችንንም የሚያጋጥመን ፈታኝ ጥያቄ በገዛ ሃገራቸው መንግስት የሚታረዱ ሲቪል ዜጎችን እንዴት እንታደግ ወይም ደግሞ ባካባቢ ያሉትን ሃገራት ደህንነት ሳይቀር ስጋት ላይ የሚጥል አመጽ ያለበት የሲቪል ህብረተሰብ የርስ በርስ ጦርነት እንዴት እናስቁም የሚሉት ናቸው።

**የሰዎችን ሰባዊ መብት መታደግን መሰረት ያደረገ ሃይልን መጠቀም ፍትሃዊ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አለኝ-** ልክ እንደ ባልካን ወይም ሌሎች በጦርነት ምክኒያት እጂግ ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች ። ሆኖም ሞራላዊ የሆነ ተግባራዊ ርምጃ በሌለበት ሁኔታ ደግሞ የባሰ ዋጋን የሚያስከፍል ጣልቃገብነትን ሊያስከትል ይችላል። ለዚህም ነው ሃላፊነት የሚሰማቸዉ ሃገራት መንግስታት ወታደሮቻቸው ግልጽ የሆነ ዓላማ ያላቸዉና ሚናቸዉንም የሚያውቁ ሰላም ጠባቂዎች እንዲሆኑ የማድረግ ግዴታ ያለባቸው ።

አሜሪካ የዓለማችንን ደህንነት የመጠበቅ ቁርጠኝነቷ ምንጊዜም የማያወላውል ጽኑ አቋም ነው። ነገር ግን በተበታተነና ራእዩም ውስብስብ በሆነው የዓለማችን ሁኔታ አሜሪካ ብቻዋን የምትጋፈጥበት ሁኔታ የለም። አሜሪካ ብቻዋን ለዓለማችን የሰላም ዋስትናን ልታረጋግጥ አትችልም። የዚህም እዉነታ በአፍጋኒስታን እየታየ ነው። ይህም እውነታ በተበታተነችው ሶማሊያ ሽብርተኝነትና ቀማኛነት ከርሃብና ከሰው ልጆች ሰቆቃ ጋር ተቀናጅተው እየታዩ ነው። እንዲሁም በሚያሳዝን መልኩ እዉነታው በሌሎች ሰላማቸው ባልተረጋጉት ሃገራት በመጭዎቹ ዓመታት መስፋፋቱ አይቀሬ ነው።

የተባበሩት መንግስታት የጦር ቃል ኪዳን ሃገራት (ኔቶ) መሪዎችና ወታደሮች፤ እንዲሁም ሌሎች በአጋርነት የቆሙ ሃይላት እላይ የተገለጸውን እውነታ ትክክለኛነት ያላቸውን አቋምና ወሳኔ በመጠቀም አፍጋኒስታን ላይ አረጋግጠዋል። ይሁን እንጂ በበርካታ ሃገራት በአገልግሎት ሰጭነት ላይ ባሉ ክፍሎች ጥረትና በተቃራኒ ወገን ባለው ተገልጋይ ሰፊ ህብረተሰብ መካከል ክፍተት አለ። ጦርነት ለምንም ተወዳጅ/ተፈላጊ እንዳልሆነ ይገባኛል፡ ነገር ግን ይህንም አውቃለሁ፤ የሰላምን አስፈላጊነት የሚያረጋግጠው እምነታችን ብቻዉን ሰላምን ለማምጣት በቂ ሊሆን አይችልም። ሰላም ሃላፊነት መውሰድን ይጠይቃል። ሰላም መስዋዕትነትን ይጠይቃል። ለዚህም ነው የኔቶ አስፈላጊነት ቀጣይነት ጥያቄ ዉስጥ የማይገባው። ለዚህም ነው የተባበሩት መንግስታትንና የሃገራትን ሰላም መጠበቅ ተልእኮን ማጠናከር ግድ የሚለንና ይህንም ሃላፊነት በተወሰኑ ሃገራት ትከሻ ላይ ብቻ እንዳንጥል የሚያደርገን። ለዚህም ነው የሰላም ማስከበርና ስልጠና ግዳጃቸው ፈጽመው ወደየሃገራቸው ለሚመለሱት ኦስሎና ጣሊያን፤ ኦታዋና ሲድኒ፤ ዳካና ኪጋሊ ላይ ክብር እየሰጠን ያለነው። -ክብር የሚናጎናጽፋቸውም እንደጦርነት ሰሪዎች ሳይሆን ለሰላም መፈጠር እንደ አስተዋጽኦ አድራጊዎች ስለምንቆጥራቸው ነው።

ሃይልን ስለመቀም አንድ የመጨረሻ ነጥብ ልናገር። ጦርነት ውስጥ ለመግባት ከባድ ውሳኔን ስንወስን በምን መልክ ጦርነቱን ማካሄድ እንደሚገባን ማሰብ ግድ ይለናል። ይህን እዉነታ የኖቤል ሽልማት ኮሚቴ የመጀመሪያዉን የሰላም የክብር ሽልማት ለሄንሪ ዳዉንት- የቀይ መስቀል መስራችና ለጄኔቫዉም ዓለም አቀፍ ስምምነት ተግባራዊነት ከፍተኛ ግፊት ያደረገው ሰው- ሲሰጥ ግንዛቤ ዉስጥ አስገብቶታል።

ጦርነት አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ቦታ ሁሉ ከሞራላዊና ስትራቴጂካዊ ፍላጎታችን አንጻር ልንከተለውና ተገዥ ልንሆንለት የሚገባ ደንብ ይኖራል። ከዚህም በላይ በአለማችን ህጋዊነትን ያልተከተሉና ጽናትን የሚጠይቁ ፈታኝ ችግሮች ሲያጋጥሙ አሜሪካ በእንዲህ አይነት ጦርነቶች ውስጥ ያላትን የላቀ ተሳትፎ ይዛ መቀጠል ይኖርባታል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። ይህም ነው በዋነኛነት ከምንዋጋቸው ጠላቶቻችን ተግባር የተለየን የሚያደርገን። ያም ነው የጥንካሪያችን ምንጭ። ለዚህም ነው ሰቆቃ የታከለበት እስር እንዲከለከል ያደረግሁት። ለዚህም ነው የጓንታናሞ ቤይ እስር ቤት እንዲዘጋ ያዘዝሁት። ለዚህም ነው አሜሪካ ለጄኔቫው ኮንቬንሽን ተገዥነቷን በድጋሚ ያረጋገጥሁት። በነኝህ አይነት አይነት ሁኔታዎችም በመግባት ራሳችንን ለመከላከል በምናደርገው ውጊያ ራሳችንን እስከማጣት እንደርሳለን። እናም ክብር እንሰጣለን- ለነኝህም አመለካከቶች ክብር የምንሰጠው ቀላል በሆኑበት ጊዜ ሳይሆን አስቸጋሪ ሆነው በተገኙበት ሁኔታ ጽኑ የሆነ ድጋፋችንን በመስጠት ነው።

ቀደም ብየ እንደተናገርሁት ጦርነትን እንደ አንድ አማራጭ ስንወስድና ስንጠቀም ለህሊናችንና ሚዛናዊ ለሆነው አመለካከታችን ክብደት ልንሰጥ እንደሚገባና ግድም እንደሚለን ገልጫለሁ። ነገር ግን አሁን ደግሞ ሳንፈልገው አሳዛኝ ዉጤቶችን የሚያስከትለውን ምርጫ ልናስወግድበት ወደምንችልባቸው ጥረቶች ልመለስና ፍትህና ዘላቂ ሰላምን ሊያመጡ ስለሚያስችሉን ሶስት ዋና ዋና መንገዶች ልናገር።

አንደኛ፡- ህግና ደንብን እየጣሱ ካሉ መንግስታት ጋር የሚኖርን ግንኙነት በሚመለከት እንደኔ እምነት የባህሪ ለውጥን ለማምጣት ለሚደረጉ የአመጽ ትግሎች አማራጭ መፍትሄዎችን ልንፈልግ ይገባናል- ማለትም ዘለቄታዊ ሰላምን የምንፈልግ ከሆነ የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ድምጽ ትርጉም ያለው ዉጤትን ሊያመጣ መቻል አለበት። ህግና ደንብን በመጣስ ላይ ያሉ ገዥዎች ለጥፋቶቻቸው ተጠያቂዎች ሊሆኑ ግድ ይላል። የማእቀብ ርምጃዎች ተገቢ ዋጋን የሚያስከፍሉዋቸው ሊሆኑ ይገባል። የማእቀብ ርምጃ ደረጃ በደረጃ እየጨመረ በሚሄድ ጫና መፈጸም ያለበት ሲሆን እንዲህ ያለውም ጫና ዉጤታማ ሊሆን የሚችለው ሌላው ዓለም በጥፋተኛው ላይ አንድ ሆኖ ሲቆም ብቻ ነው።

ከላይ ለገለጽሁት አንድና አስቸኩዋይ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው የኒዩክሌር ጦር መሳሪያ ስርጭትን ለመግታት እየተደረገ ያለው ጥረትና ከኒዩክሊየር ጦር መሳሪያ የጸዳች ዓለምን መፈለጋችን ነው። ባለፈው ክፍለዘመን አጋማሽ የዓለም መንግስታት ራሳቸዉን ግልጽ በሆነ የህግ ማእቀፍ ለማስተዳደር ስምምነት አድርገዋል፡- ሁሉም ሃገራት የኒዩክሌር ሃይልን ሰላማዊ ለሆነ ጥቅም ማዋል የመቻል፤ የኒዩክሌር ሃይል የሌላቸው መንግስታት ምንም ማድረግ የማይችሉ ሲሆን የኒዩክሌር ሃይል ያላቸው መንግስታት ደግሞ የኒዩክሌር ሃይል መጠቀም እንዲወገድ ጠንክረው ይሰራሉ። እኔም ይህንን የህግ ማእቀፍ ለማክበርና ለመጠበቅ ቆርጬ የተነሳሁ ነኝ። ይህም የሃገሬ የዉጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሚያጠነጥንበት ማእከላዊ ነጥብ ነው። በመሆኑም ከፕሬዘዳንት ሜድቬድቭ ጋር በጋራ አሜሪካና ሩሲያ የኒዩክሌር የጦር መሳሪያ ቅነሳ በሚያደርጉበት ሁኔታ እየሰራሁ ነው።

ነገር ግን ልብ ልንለው የሚገባ ጉዳይ ሁላችንም እንደ ኢራንና ኮሪያ ያሉ መንግስታት ይህን የህጋዊ ማእቅፍ ስርአት የሚያበላሽ ጨዋታ እንዳይጫወቱ ለማድረግ ያለን አቋዋም ጽኑ መሆን የሚገባው መሆኑን ነው። የዓለም ዓቀፍ ህግጋትን የሚያከብሩ መንግስታት እንዲህ አይነት ተግባራትን ባንክሮ ይከታተላሉ። የሃገራቸው ደህንነት ስጋት ላይ እንዳይወድቅ እየታገሉ ያሉ መንግስታት ደግሞ በመካከለኛው ምስራቅና በምስራቅ እስያ እየተደረገ ያለውን የጦር መሳሪያ እሽቅድምድም በቸልታ የሚመለከቱት አይደለም። ቀሪዎቹ ሰላም ፈላጊ መንግስታት ደግሞ ሌሎች መንግስታት ራሳቸዉን በኒዩክሌር የጦር ማሳሪያ በማስታጠቅ ስራ ላይ ተጠምደው ሲያዩ እንዲሁ ዝም ብለው ሊመለከቱት አይችሉም።

ከላይ የጠቀስሁት መርህ ዓለም አቀፍ ህግጋትን በመጣስ የራሳቸውን ዜጎች ለሰቆቃ ለሚዳርጉ መንግስታትም ላይ የሚሰራ ነው። በዳርፉር የዘር ማጥፋት ተግባር ሲከናወን፤ ስልታዊ የሆነ አስገድዶ መድፈር በኮንጎ፤ አይምሮን የማሰቃየት ተግባር በቡርማ- እነኝህ ሁሉ ተግባራት የሚያስከትሉዋቸው ችግሮች አሉ። አዎ ሃላፊነት የሚጠይቅ ስራ ይኖራል፤ አዎ የዲፕሎማሲ ስራም ይኖራል- ነገር ግን እነዚህ መንገዶች ተግባራዊ መሆን ካልቻሉ ችግር መከሰቱ የግድ ነው። እናም ሁላችንም በመደጋገፍ በጋራ በቆምንበት ሁኔታ ለችግሮች መፍትሄ ለማፈላለግ ባለው ጣልቃገብነትና ችግር ፈጣሪዉን በመደገፍ መካከል ለሚኖረው የምርጫ አጣብቂኝ የመጋለጣችን ሁኔታ በእጂጉ ይቀንሳል።

ከላይ የጠቀስሁት ሃሳብ ወደ ሁለተኛው ነጥቤ ያመጣኛል- የምንፈልገው ሰላም ምን ይመስላል ወደሚለው።ሰላም የሚታይ ብጥብጥ አለመኖር ማለት አይደለም። ፍትሃዊ ሰላም ዘላቂነት የሚኖረው በእያንዳንዱ ግለሰብ ተፈጥሮዓዊ መብቶችና ክብር ላይ የተገነባ ሲሆን ነው።

## የግንቦት 7 ንቅናቄ በአውስትራሊያ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር እጅግ የተሳካ ስብሰባ አካሄደ

ኢትዮጵያ አገራችንን ታይቶ በማይታወቅ እብሪትና ዘረኛነት እየገዛት ያለውን የወያኔ ቡድን በተባበረ ህዝባዊ ትግል ለማስወገድ እንዲቻልና በምትኩ በምርጫ ህግ የህዝብ አመኔታና ፈቃደኝነት ያገኘ የመንግሥት አስተዳደር ሥር ዓት ለማስፈን ራዕይ ሰንቆ የተነሳው የግንቦት 7 ንቅናቄ፤ በፍትህ እጦት ምክንያት በመላው አለም ተበትኖ የሚኖረውን ሁሉ በትግሉ ለማሳተፍ የሚያደርገውን አለም አቀፍ ጥረት በመቀጠል ካለፈው ሳምንት ጃንዋሪ 2 ጀምሮ በአውስትራሊያ የተለያዩ ከተሞች ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል።

በንቅናቄው ሊቀመንበር በዶ| ር ብርሃኑ ነጋ ሰብሳቢነት እየተካሄደ ያለው ይህ ስብሰባ ባለፈው ቅዳሜ ጃንዋሪ 2 በሜልቦርንና አካባቢው ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር በማግሥቱ ዕሁድ ጃንዋሪ 3 ደግሞ በስዲኒ ከተማ ከሚኖሩ ወገኖቻችን ጋር ከ8 ሰዓት በላይ የፈጀ ውይይት አካሂዶአል። በሁለቱም ከተሞች በተካሄዱት በነዚህ ስብሰባዎች ቁጥሩ እጅግ የበዛ ህዝብ የተሳተፈ ሲሆን እስከ ዛሬ ለፖለቲካ ስብሰባ ይወጣ ከነበረው ህዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር የመጀመሪያ ሪኮርድ እንደሆነ በሁለቱም ከተሞች ከ20 አስከ 30 አመት የኖሩ ምስክርነታቸውን ለግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ሰጥተዋል።

ስለ ግንቦት 7 አላማና ራዕይ አንዲሁም የትግል ሥልት በስፋት ያስረዱት ዶ/ር ብርሃኑ በሁለቱም ከተሞች ለተሰበሰበው ተሰብሳቢ በቂ ማብራሪያ ከመስጠታቸውም በላይ ወያኔ የአገራችንን ዳርድንበር ለምን ለጎረቤት ሱዳን ቆርሶ መስጠት እንዳስፈለገውና ይባስ ብሎም ለም የሆነውን የእርሻ ቦታዎች በርካሽ ዋጋ ለምን ለባዕዳን መቸብቸብ እንደተያያዘ በስፋት ካብራሩ ቦኋላ ይህንን ጸረ ህዝብና ጸረ አገር ድሪጊት በአስቸኳይ ማስቆም የዚህ ትውልድ አደራ እና ሃላፊነት እንደሆነ ገልጸዋል። በዚህም ምክንያት የአገሬ ጉዳይ ይመለከተኛል፡ ነጻነትና ፍትህ ወያኔ በቸርነቱ የሚሰጠን ሲያሻው የሚነፍገን ሳይሆን ተፈጥሮ የለገሰቺን መብታችን መሆኑ የሚሰማው ሁሉ ትግሉን በመቀላቀል የወያኔን ዘረኝነት እድሜ ለማሳጠር መስራት አለበት ሲሉም የትግል ጥሪ አቅርበዋል። በአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ስላለው መከፋፈል፤ መጎነታተል፤ ወዘተ በርካታ ጥያቄዎች ቀርበው በቂ ምላሽ ከተሰጣቸው ቦኋላ ብዛት ያላቸው ሰዎች የግንቦት 7 አባልነት ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ንቅናቄውን የተቀላቀሉ ሲሆን የግንቦት 7 ድርጅታዊ መዋቅር በሁለቱም ከተሞች እንደተዘረጋና ለትግሉ ማጠናከሪያ የሚሆን ገንዘብም እንደተሰባሰበ ለማወቅ ተችሎአል። የግንቦት 7 ሊቀመንበር በአውስትራሊያ የሚያደርጉትን ተመሳሳይ ሥራ በመቀጠል የፊታችን ቅዳሜ ጃንዋሪ 10 በፔርዝና አካባቢው ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር እንደሚሰበሰቡ ና በዚያም የግንቦት 7 ድርጅታዊ መዋቅር እንደሚመሰርቱ ከህዝብ ግንኙነት የተገኘው ዜና ያመለክታል።

## ወያኔ ሰራዊት ለመቅጠር ማስታወቂያ ... ከገጽ 1 የዞረ

ህዝባዊ ድጋፍ የሌለው ወያኔ እስከዛሬ ድረስ ሙሉ እምነቱን በሰራዊቱ ላይ ጥሎ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከግንቦት97 ምርጫ በሁዋላ ግን ከአጋዚ ሰራዊት በስተቀር በሌሎች የሰራዊት አባላት ላይ ያለው እምነት እየተሸረሸረ መጥቷል። ከ97 ምርጫ በሁዋላ በሶማሊያና በሶማሊያና በኦጋዴን አካባቢዎች ሁለት የተለያዩ ጦርነቶችን ያደረገው ወያኔ፣ በሶማሊያ በአሳፋሪ ሽንፈት ተገዶ እንዲወጣ ሲደረግ፣ በኦጋዴን ደግሞ በሁለት ሳምንት ውስጥ አካባቢውን ነጻ አወጣለሁ ብሎ እንዳልፎከረ፣ እስከዛሬ ድረስ ጦርነት በማካሄድ ላይ ነው። እነዚህ በቅርቡ የተደረጉት ሁለት ጦርነቶች የወያኔን ሰራዊት ብቃት መዳከም እንደሚያመልክቱ የተለያዩ አለማቀፍ ትንተናዎች ሲሰጡ መቆየታቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ከእነጄ/ል ተፈራ ማሞ ጋር ተዛምዶ በብአዴን የሰራዊት አባላት ውስጥ የተነሳው ንቅናቄም ለወያኔ ጦር መዳከም ተጨማሪ ምክንያት ሆኖአል።

ወያኔ በአሁኑ ሰአት በጥቂት የትግራይ ተወላጅ ሰራዊት አባላት ብቻ እንደሚመካ የጠቀሰው ሪፖርት፣ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የሶማሊና የሌሎችም ክልሎች የሰራዊት አባላት አብዛኞቹ ለእንጀራ ሲሉ እንጅ ከልብ አምነው ወያኔን እንደማይደግፉ ማወቁ፣ ምልመላውን በተለይ በትግራይ ክልል ላይ እንዲያነጣጥር እንዳስገደደው ሪፖርተራችን መረጃዎችን ዋቢ አድርጎ ገልጿል። በትግራይም ቢሆን ወጣቶቹ ከድሮው በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ መገኘታቸውና በህወሀት አካሄድ ደስተኛ ባለመሆናቸው እንደቀደሙት ጊዜያት ሰራዊቱን በፍላጎትና በፍቅር የሚቀላቀሉበት ሁኔታ እንደሌለ ዘገባው አክሎ አስረድቷል።

በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ጥቂት የትግራይ አዛዦች በማዘዢያ ማማዎች ላይ ተንጠላጥለው አብዛኛውን የሌሎች ክልል የሰራዊት አባላት እንደበግ የሚነዱበት ሁኔታ ማብቃት እንዳለበት ሰራዊቱ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ሲያነሳ መቆየቱ ቢታወቅም፣ እስካሁን ድረስ ወያኔ ለሰራዊቱ ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንዳልቻለ ዘገባው አስታውሷል። እንዲያውም ይባስ ብሎ የትግራይ ተወላጅ የሰራዊት አባላት እስካሁን ከነበረውም በባሰ ሁኔታ እንደ ማጣፊጫ ቅመም በሰራዊቱ ውስጥ እየተበተኑና መመሪያ እየሰጡ መገኘታቸውን ዘገባው አመልክቷል።

በሰራዊቱ ውስጥ አብዮታዊ ዲሞክራሲንና የህገመንግስት የበላይነትን ለማስተማር በሚል ሰሞኑን የተጀመረው እንቅስቃሴ፣ የሰራዊቱን የልብ ትርታ ለማወቅ ታስቦ የተደረገ ቢሆንም፣ ወያኔ ከሰራዊቱ የሚያገኘው መልስ ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ ወታደር ለመመልመል እንደተገደደ ዘገባው አጠቃልሎአል።

## በወያኔው የይስሙላ ፍርድ ቤት ከርቼሌ የተወረወሩት እነ ጀነራል ተፈራ ማሞ ከሌሎች እስረ ኞች ጋር እንዳይገናኙ ክልከላ ተደረገ

ከግንቦት 7 ጋር መንግሥቴን ልትገለብጡ ዶልታችኋል በሚል ሰበብ አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቅርቡ ሞትና እድሜልክ የተፈረደባቸው የመከላከያ ሴራዊቱ አባላትና ሲቪሎች፣ በእስርቤት ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች እስረኞች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንዳያደርጉ ትእዛዝ እንደተሰጣቸው ከእስርቤት የደረሰን መረጃ አመልክቷል፤ ትእዛዙን ጥሰው ለመገናኘት የሞከሩ ሌሎች እስረኞች ደግሞ ወደ ሸዋ ሮቢትና ዝዋይ እንደሚላኩ ታውቋል።

መረጃው እንደሚጠቁመው በተለያየ ምክንያት በወያኔ ወህኒ ቤት ታስረው የሚገኙ እስረኞች ከነዚህ የዕድሜ ይፍታህ ፍርደገምድላዊ ውሳኔ ከተላለፈባቸው የፖለቲካ እስረኞች ጋር እንዳይ ነጋገሩ እገዳ የተጣለባቸው በመሆኑና ይህ በ እስርቤቱ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቀው እብሪታዊ ውሳኔ ብዙዎችን በማስቆጣቱ አጋጣሚውን ያገኙት እስረኞች ትእዛዙን በመጣስ "አታናግሩዋቸው" ከተባሉት ጋር በ እልህ እንደተነጋገሩና በዚህም የተነሳ የተወሰኑት እስረኞች ተመርጠው ወደ ሸዋ ሮቢትና ዝዋይ እንዲላኩ መደረጋቸውን ለማወቅ ተችሎአል። በዝዋይና ሸዋ ሮቢትም ከደረሱ ቦኋላ አሰቃቂ ድብደባ እንደተፈጸመባቸው የደረሰን መረጃ ዜና ያመለክታል።

ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ እስረኞቹ በ እነርሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ሆነው እያሉ ምን አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው እንደተፈሩና ከሌሎች ጋር እንዳይገኛኙ እንደተከለከሉ ለምንስ የወያኔ ታማኝ ጠባቂዎች 24 ሰአት በአይነቁራኛ እንደከታተሉዋቸው መደረጉ ነው የሚሉት የመረጃ ምንጮች፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግንቦት የሚለው ስም ራሱ ወያኔን በቁም የሚያባንነው ሆኖአል በማለት በመላው አገሪቱ የግንቦት 7ን እንቅስቃሴ ለመከታተል እየተላለፈ ያለውን የውስጥ መረጃ ብዛትና አይነት ገልጸዋል።

ወያኔ፣ ከግንቦት 7 ጋር በተያያዘ የተከሰሱ ሰዎች ከማንኛውም እስረኛ ጋር እንዳይቀላቀሉ ማድረጉ ፣ አገዛዙ በህዝብ የተወለደውንና ህዝባዊ ድጋፉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን ንቅናቄ በእጅጉ መፍራቱን ያሳያል የሚሉ አስተያየቶችም ተሰጥተዋል። በእስር ቤት ውስጥ በግፍ ታስረው የሚገኙት ኢትዮጵያውያኑ፣ በእየለቱ የሚያሳዩት ጠንካራ አቋም፣ የወያኔ አለቆችን በእጅጉ እያበሳጨ እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሎአል።

## የወያኔው አገዛዝ ሰፊ የሆነውን የአገራችንን መሬት ለሱዳን ለመስጠት የሚያደርገውን ሽርጉድ የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በጥብቅ አወገዘ፣ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብም ጥሪ አቀረበ

ኮሚቴው ታህሳስ 22 ቀን 2002 ዓም ባወጣው መግለጫ የኢትዮጵያ ህዝብ በስተጀርባው የሚደረግና የራሱን ጥቅም የማያስጠብቅ ምንም አይነት ስምምነት እንደማይቀበል ገልጾ፣ በታዛዥነት ስሜትና በጊዜያዊ ጥቅም ታውረው በዚህ የአገርን ከፍተና ጥቅም አሳልፎ በሰጠ ስምመነት የተሳተፉ፣ ድርጊቱን በመቃወም ፈንታ በአካልም ሆነ በፊርማ ወይም በሁለቱ መንገድ የተሳተፉ ኢትዮጵአውአን ሁሉ በግልም ሆነ በጋራ፣ በታሪክና በህግ ፊት በአገር ክህደት ወንጀል ተጠያቂ መሆናቸውን አጥብቀው ሊገነዘቡት ይገባቸዋል ሲል አስጠንቅቋል።

የወያኔው አገዛዝ የትግራይን ህዝብ ከአገር ክህደቱ ጀርባ ለማሰለፍና ከሌሎች ህዝቦች ጋር ለማጋጨት የፈጠረውን ዘዴም የድንበር ኮሚቴው አጥብቆ ኮንኖአል። ኮሚቴው ጉዳዩን ሲያብራራም "ምንም እንኳ የትግራ ህዝብ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን መሰጠቱን ደግፎ ተሰለፈ፣ ዳንኪራ ረገጠ ብሎ ለማመን ቢቸግርም፤ ወያኔ የትግራይን ህዝብ ተጠቅሞ የሚያከናወነውን ተንኮል የአሁኑ የክህደት ጉባኤ መድረክ የበለጠ አጉልቶታል። በአሁኑ ወቀት የትግራይ ህዝብ ወራሪዎችን እያወደሰና እየጨፈረ እንዲቀበል ማድረግና ያን ትርኢት ለኢትዮጵያ ህዝብ ማቅረብ መለስ ዜናዊ የትግራይን ህዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖች ጋር ለማቀያየምና ለማዳማት የሚያደርገው ከፍተኛ ሴራና ወንጀል ልዩ ምእራፍ እየያዘ መምጣቱን ነው።"" ብሎአል።

የድንበር ኮሚቴው በስተመጨረሻም " ወያኔ በአገራችን ላይ የሚያደርገው ከፍተኛ ክህደትና ሴራ ረገብ ማለት አልቻለም። ሌሎቻችን ደግሞ የአለፉት አባቶቻችን በብዙ መስዋትነት ያስተላለፉልንን አገር ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ ግዴታ አለብን። ለዚህም ተቀዳሚው ተግባር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በግልም ሆነ በጋራ የወገናችንን ስቃይና መከራ ከዚያም የወያኔን የክህደት ወንጀልና መሰሪነት ጠልቆ ሊሰማን ይገባል። ከዚያም በማከታተል በምንችለው መንገድና ቀዳዳ ሁሉ ለሌሎች ኢትዮጵያውያንና ኣለም አቀፍ ተቅዋማትና መንግስታት የህዝባችንን እሮሮ በጉልህ ማሰማት ይገባናል።" ሲል ጥሪ አቅርቦአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን** g7radio@ginbot7.org ***ወይም*** በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661